# የዘወትር ጸሎት

በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርተ መስቀል፥ ፊቴንና መላ ሰውነቴን ሦስት ጊዜ አማትባለሁ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አሜን (3) ጊዜ።

አንድ አምላክ በሚሆን፥ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም፥ ንጹህ ልዩ ክቡር ጽኑይ በሆኑ በሦስትነት ወይም በሥላሴ እያመንኩና እየተማጸንኩ፥ ጠላቴ ሰይጣንን እክድሃለሁ። በዚች በእናቴ በቤተ ክርስቲያን ፊት ቆሜ እክድሃለሁ። ለዚህም ምስክሬ ማርያም ናት። በዚህም አለም፥ በወዲያኛውም አለም፥ እርሷን አንባ መጠጊያ አድርጌ እክድሃሉሁ።

አቤቱ እናመሰግንሃለን፥ አቤቱ እናከብርሃለን፥ አቤቱ እንገዛልሃለን፥ አቤት ቅዱስ ስምህን እናመሰግናለን፥ ጉልበት ሁሉ የሚሰግዱልህ፥ አቤቱ እንሰግድልሃለን፥ አንደበት ሁሉ ላንተ ይገዛል፥ የአምላኮች አምላክ፥ የጌቶች ጌታ፥ የንጉሦች ንጉሥ አንተ ነህ። የሥጋም የነፍስም ፈጣሪ አንተ ነህ። እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ቅዱስ ልጅህ እንዳስተማረን እንጠራሃለን።

# አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ፥ በሰማይ የምትኖር፥ ስምህ ይቀደስ፥ መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን። የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ፥ በደላችንን ይቅር በለን፥ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥ አቤቱ ወደ ፈተናም አታግባን፥ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፥ መንግሥት ያንተ ናትና| ኃይል፥ ክብር፥ ምስጋና ለዘለዓለም አሜን።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፥ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን። በሃሳብሽ ድንግል ነሽ፥ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ! ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል። ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፥ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነዉ። ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነዉና። ከተወደደዉ ልጅሽ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና ምህረትን ለምኝልን ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ። ለዘለዓለም አሜን።